- እጅ በማውጣት ተማሪዎች በመምርጥ ፊት ወጥተው ዘምሩ

ከላይ በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ የተጻፈውን እንመለከት

ከላይ በሙዚቃ መፃፊያ ላይ የተጻፈው መዝሙር አራት ስንኝ ያለው መዝሙር ነው። እሱንም በስንኝ ከፍለን እናየዋለን።

ወንድሜ ያዕቆብ ወንድሜ ያዕቆብ--------------ስንኝ አንድ

ተኛህ ወይ ተኛህ ወይ ----------------------------ስንኝ ሁለት

ደወል ተደወለ --------------------------------------ስንኝ ሶስት

ተነሳ ተነሳ--------------------------------------------ስንኝ አራት

ተማሪዎች እስኪረዱ ድረስ የመጀመሪያውን ስንኝ ደጋግመን ማዘመር ይጠበቅብናል ፤ የቀረውን ስንኝም ልክ እንደዛው ስንኝ በስንኝ እያከፋፈለን ማስዘመር መቻል አለብን።

በመቀጠልም ሁሉን ስንኝ አንድ ላይ አያይዘን በስልተምት ውስጥ ሆነን ማስዘመር አለብን። ከዛ በኋላ እጃቸውን እያጨበጨቡ እንዲዘምሩ ማድረግ አለብን።

**ለምሳሌ፡-** በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ላይ ቀጭን ቁልፍ አስቀምጠን በዛላይ ሙዚቃ እፅፋለን እንማራለን።


ወንድሜ ያዕቆብ



## 2.2.3. የኪነንድፍ አይነቶች

## 1. የቁሳቁስ ንድፍ

የቁሳቁስ ንድፍ (ስትሊፍ ድሮይንግ) የምንለው የማይነቃነቅ ሕይወት አልባ አብዛኛውን ጊዜ ግዑዝ የሆኑ ቁሳቁሶችን ስንሰራ፣ ለምሳሌ ተፈጥሯዊ (ምግብ ፣ አበባ ፣ የሞቱ እንስሳት ፣ ዕፅዋት ፣ አለቶች ወይም ዛጎሎች) ወይም ሰው ሰራሽ (የቤት ውስጥ ቁሳቁሶች፣ መጻሕፍት ፣ የአበባ ማስቀመጫዎች ፣ ጌጣጌጦች ፣ ሳንቲሞች ፣ ቧንቧዎች እና የመሳሰሉት) ።



*ምስል 19 የቁሳቁሶችን ንድፍ*

***<u>የተግባር ሥራ -19</u>***

1.በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሳቁሶችን፣ አበባ ወይም ዕፅዋት በጥሩሁኔታ በመደርደር ተማሪዎችን በመረጡት የንድፍ ስነዘዴ በመጠቀም እንዲሰሩ ያድርጉ?

## 2.3. በትያትር ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶ ሃሳብን መግለጽ

*የክፍለ ግዜ ብዛት (12)*

*መግቢያ*

ትያትርን ፣ በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶ በቡዙ ነገር መግለጽ ሲለምችሉ ተማሪዎች በዚህ ትምህርት ክፍል ላይ ሀሳባቸውን እንዴት መግለጽ እዳለባቸው በተገቢው መማር ይጠበቅባቸዋል፡፡ በትያትር ሊገለፅ የማይቻል ሀሳብ የለም ማለት እንችላለን፡፡ የማህበረብን እና የግለሰቢን ሀዘን ፣ ደስታ ፣ ችግር ውጣውረድ እና የተለያዩ ነገርን በተንቀስቃሽ ምስልና በፎቶ ሀሳብን መግለጽ እንደምቻል በቂ ግንዛቤ እና እውቀት መኖር ያስፈልጋል፡፡

**አጥጋብ የችሎታ ደረጃ**


- ትያትርን በተንቀሳቃሽ ይገልፃሉ
- በፎቶ ምስል ፈጠራዊ ሃሳብን ይዘረዝራሉ
- ትውንና በፎቶ ምስል በመተቀም ፈጠራዊ አገላለጽ ያስረዳሉ

**የመማር ማስተማር ሥነ ዘዴዎች**

- ትያትርን በተንቀሳቃሽ ማሳየት
- በፎቶ ምስል ፈጠራዊ ሃሳብን መዘርዘር
- ትውንና በፎቶ ምስል ፈጠራዊ መግለፅ

**የትምህርት መርጃመ ሳሪያዎች**

- መለማመጃ ክፍል
- ምስሎች የድምጽ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወት
- እርሳስ ፣ ማስመሪያ ፣ከሰል፣ ከረዮን እና በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶች
- የተቀረጹ ድምፅ እና ምስሎች
- ጽሁፎች እና የመሳሰሉት



*ምስል 40 ለጋብቻ እና ለበዓላት የሚያገለግል ከበሮ (ካራቤ)*

ይህ በምስል ላይ የሚታየው የሙዚቃ መሳርያ ከሽክላና ከተለያዩ ከእንስሳት ቆዳዎች የምሰራ መሳርያ ሲሆን ለሰርግና ለአንዳንድ አስደሳች ነገር ሲኖር ይጠቀማሉ፡፡



*ምስል 41 ሁለቱም በኩል እኩል የሆነ ከበሮ*

ይህ ከላይ በምስል የሚታየው ሁለቱም በኩል እኩል የሆነ ምት የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ ይህ ከበሮ የሚሰራውም በተለያዩ ከእንስሳት ቆዳና ከእንጨት ነው፡፡ በአብዞኛው የሚጠቀመውም ለመንፈሳዊ አገለግሎት የሚያገለግል የምት መሳሪያ ነው፡፡

በድምጽ አወራረድ መሠረት ተዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ወይም ከተፍተኛ ወደ ዝቅተኛ በጥነቃቀ እቦታቀኝ የድምጽ ፍጥነት ሳያዛባ የሚከናወን ይሆናል፡፡ ማይራ በዋናነት የሚጨዋቱት ወጣት ወንዶች ሲሆኑ እጨዋወቱም በከንፈር ላይ አስቀምጠው ከግራ ወደ ቀኝ ወይም ከቀኝ ወደ ግራ በማመላለስ በትንፈሽ በመንፋት ነው፡፡

- ✓ **ካሳ**

ይህ ከትንፋሽ የሙዚቃ መሳርያዎች አንዱ ነው፡፡ ካሳ ከጎሽ ከንድ የሚበጅ የደራሽ የሙዚቃ መሳሪያ ነው፡፡ቀንድ በሾለ በኩል ጫፍ አከባብ በጎን ተበስተዉ አገለግልሎት ላይ ይውላል፡፡ ባህሉን ጠንቅቀዉ የሚያቁ ሰዎች ልዩ ክብር ያለው የትንፋሽ መሳሪያ ነው፡፡ የመንፋት ስርዓት በራሱ በባህላዊ አገባብ በክብር ማሰማት (ከካሳፖኑሲሳ) መንፋት አይባልም፡፡ ካሳ በደራሽ ባህል በተላይ የእናብ አባት (ዳማ)ሲሞት በተለየሁነታ ጠቅም ላይ እንደምውል ይናገራሉ፡፡

- ✓ **ሎላታ**

ይህ የሙዚቃ መሳርያ በክልላችን ውስጥ በደራሽ አከባብ የምገኝ የሙዚቃ መሳርያ ሲሆን በአከባብያቸውም ታዋቅ የሆነ የሙዚቃ መሳርያ ነው፡፡ የሚሰራዉም ከተለያዩ ከእንስሳ ቀንድና ከጠንካራ እንጨት የሚዘጋጅ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳርያ ነው፡፡ ከላይ እስከ ታች ውስጡ ሙሉ ክፍት  የሆነና በአፉ በኩል ጠበብ ያለእና ታች በኩል ሰፋ ብሎ የሚሰራ ነዉ፡፡ የላኛው ስፋቱ 7 ሰንት መትር የታቸኛው ስፋት 5 ሰንት መትር እና ቁመቱ 40 ሰንት መትር ርዝመት አለው፡፡ ይህን መሳርያ በመጠቀም በበዓላት ጊዜ በውዝዋዜ ያደምቃሉ፡፡ ውጫዊ በኩል የሚገጠዉ የሚያበለጭልጨው ብረትና ቆዳ የተሰራ ሲሆን የሚጫወቱትም ወንዶች ብቻ ናቸው፡፡

- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ምሳሌዎችን እና ምልክቶችን ሰርተው ያሳያሉ፡፡
- አካባቢያዊ የትወና እና የእይታ ጥበባትን በመዝሙር በትያትር ጥበባት፣ በተንቀሳቃሽ ምስል እና በፎቶ አማካኝነት ሰርተው ያቀርባሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ስነ ዘዴዎች

- አካባቢያዊ የእይታ ጥበባትን እና በፎቶ አማካኝነት እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- ኪነንድፍ እና ባለቀለም የወረቀት ሞዛይክ በመጠቀም ባህላዊ እና ታሪካዊ ምስሎችን እንዲሰሩ መንገድ ማሳየት፡፡
- በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ምሰላዎችን እና ምልክቶችን እንዲሰሩ ማበረታታት፡፡

## የትምህርት መርጃመ ሳሪያዎች

- መለማመጃ ክፍል
- ምስሎች እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻ
- እርሳስ ፣ከሰል፣ ከረዮን እና በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶች

## የግምገማና ክትትል ስልት

- ምልከታ
- የግል ገለጻ
- የቡድን ገለጻ
- ማህደር ኣያያዝ
- የቃል ጥያቄ
- የጽሑፍ ጥያቄ

***<u>የማነቃቂያ ጥያቄ -3</u>***

1. በአከባቢያችው የሚገኝ የቤት አሰራር ሁኔታ እንዲያብራሩ ያመቻቹ፡፡

- እርሳስ ፣ከሰል፣ ከረዮን
- የተቀረጹ ድምፅ እና ምሽሎች
- አርማ፣ የማስታወቂያ ምስሎች እና በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶች

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ምልከታ
- የግል ገለጻ
- የቡድን ገለጻ
- ማህደር ኣያያዝ
- የቃል ጥያቄ

***<u>የማነቃቂያ ጥያቄ -1</u>***

1. የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለው መስተጋብር እንዲያብራሩ ማድረግ?

2. ጥንድ ጥንድ በመሆን «የአየር ንብረት ለውጥ» ሀሳብ ላይ እየተነጋገራችሁ ዘርዝረው እንድያብራሩ ማድረግ?

**መልስ**

1. ተማሪዎች ተራ በተራ እየጠየቁ ትክክለኛ መልስ የመለሰውን መደገፍ
2. ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ እንድወያዩ ማመቻቸት

## 4.1. የትውን እና የእይታ ጥበባትን በመጠቀም ጠቃሚ ሀብቶችን ከመጠበቅ እና ከመንከባከብ ጋር ያለው መስተጋብር

*የክፍለ ግዜ ብዛት (10)*

**መግቢያ**

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተውንና የእይታ ጥበብን በመጠቀም በአከባቢያቸው ያለው ጠቃሚ ሀብቶችን በአገባቡ እንደት መጠበቅና መንከባከብ እንዳለብን ያስረዳል። በመሆኑ ማህበረሰቡ ሀብቶቻቸውን እንክብካቤና ጥበቃ

በማድረግ ከትውልድ ወደ ትዉልድ እንዲተላለፍ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች በአከባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብቶቻቸውን በአግባቡ በመጠበቅና በመንከባከብ ለማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ በመዝሙር እና በውዝዋዜ በመጠቀም ጠቃሚ ሀብቶችን ማህበረሰቡ እንዲጠብቅ ማስተላለፍ እንዳለባቸው ይታመናል፡፡ ስለሆነም በአከባቢያቸው የሚገኙ ማናቸውም ጠቃሚ ሀብቶችን በአግባቡ መጠበቅና መከባከብ አስፈላጊ ስለሆነ ለሀብቶች ልዩ ጥበቃ ማድረግ ትልቅ ሀላፍነት በመሆኑ ሁላችንም ጠቃሚ ሀብቶችን መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መሠረት ተማሪዎች ከላይ የተዘረዘሩትን ጠቃሚ ሀብቶችን ለመጠበቅ ለመንከባከብ በመዝሙር ፣ በስዕል በተንቀሳቃሽ ምስሎች አማካይነት የራሳቸውን ተሳትፎ በማድረግ ሌሎችንም ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡

## አጥጋቢ የችሎታ ደረጃ

- የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን እንዲሁም ከወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳዮች ጋር መስተጋብራዊ ስራዎችን መስራት ይችላሉ፡፡
- ሰርቶ ማሳየት እና ጉብኝት ያከናውናሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ስነ ዘዴዎች

- የትውን እና የእይታ ጥበባትን ከሌሎች የትምህርት ዓይነቶች ጋር ያለውን እንዲሁም ከወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳዮች ጋር መስተጋብራዊ ስራዎችን መስራት
- ሰርቶ ማሳየት እና ጉብኝት

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- መለማመጃ ክፍል
- ምስሎች የድምጽ እና ተንቀሳቃሽ ምስል ማጫወቻ

- የተቀረጹ ድምፅ እና ምስሎች
- አርማ ፣ የማስታወቂያ ምስሎች እና በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶች

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ምልከታ
- የግል ገለጻ
- የቡድን ገለጻ
- ማህደር ኣያያዝ
- የቃል ጥያቄ

**ጠቃሚ መረጃ**

ጠቃሚና ውድ ሀብቶች የሚንላቸው የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ልሆኑ ይችላሉ፡፡ የተፈጥሮ ሀብቶች የምንላቸው ውሃ ፣ አየር፣ እጥዋት ፣ ማዕድናትና ሌሎች ሲሆኑ ሰው ሰራሽ ሀብቶች የሚንላቸው መሰረተ ልማቶች ፣ ኤሌትሪክ ፣ የመንገድ ልማት ፣ ትምህርት ቤቶች ፣ ጤና ተቋማት እና ሌሎች ህዝብ የሚገለግሉባቸው ናቸው፡፡ እነዚህ ጠቃሚ ሀብቶች እርስ በእርስ የተጣመሩና የተያያዙ ናቸው፡፡ አንዱን ስንከባከብ እና ስንጠብቅ ሌላውን ከመጥፋት እንጠብቃለን፡፡ እንዲሁም አንዱን መጠበቅና መንከባከብ ካልቻልን በተዘዋዋሪ ሌሎችን እንጎዳለን፡፡

## በትውን እና እይታ ጥበባት ከሳይንስ ትምህርት ጋር ዝምድና

የትውን እና እይታ ጥበባት ከምናስበው በላይ በትክክለኛው መንገድ ጥቅም ላይ ሲውል, አንዳንድ ከባድ እና ጠቃሚ የሳይንስ ሀሳቦችን በደንብ ያስተላልፋል፡፡ በመደበኛነት ሊታዩ የማይችሉ ረቂቅ ሀሳቦችን ለመቅረጽ እና ተማሪዎች ትርጉም እንዲፈጥሩ ያግዛሉ፡፡ ተማሪዎች በሳይንሳዊ ሀሳቦች እንዲወያዩ እና እንዲያመዛዝኑ እድል ይስጡ፡፡

*መምህራንን ተማሪዎችን ያሳትፉ እና ያበረታቱ በማስተማር ውስጥ ፈጠራ!*

**የትምህርት መርጃመ ሳሪያዎች**

- መለማመጃ ክፍል
- ምስሎች የድምጽ እና ተንቀሳቃሽ ምሽል ማጫወቻ
- እርሳስ ፣ከሰል፣ ከረዮን
- የተቀረጹ ድምፅ እና ምሽሎች
- አርማ፣ የማስታወቂያ ምስሎች እና በአካባቢው የሚገኙ ቁሳቁሶች

**የግምገማና ክትትል ስልት**

- ምልከታ
- የግል ገለጻ
- የቡድን ገለጻ
- ማህደር ኣያያዝ
- የቃል ጥያቄ

***<u>የማነቃቂያ ጥያቄ -2</u>***

1. ተማሪዎች በአከባብያችዉ ለአካል ጉዳተኝነት ሊያጋልጡ የሚችሉ ነገሮችን ተወያይተዉ እንድገልጹ አድግጓቸዉ?

***<u>መልስ</u>***

1. ተፈጥሯዊ እና ሰውሠራሽ

**ጠቃሚ መረጃ**

አካል ጉዳተኝነት ማንኛውም ሰው ሊያጋጥመው የሚችል ተፈጥሮአዊም ሆነ ሰው ሠራሽ አደጋ ውጤት ነው። እንደምናውቀው አካል ጉዳተኝነት የሰው ልጆች አኗኗር አንዱ ገጽታ ነው። አካል ጉዳተኝነት ስላልፈለግነው የሚቀር ሳይሆን፣ ባጋጣሚ የሚመጣ መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።

